"ሀብታም የመሆን ሳይንስ አለ፤ እሱም እንደ አልጄብራ ወይም የሂሳብ አይነት ትክክለኛ ሳይንስ ነው። ማንኛውም ሰው ሳይንሱን ቢማር በእርግጠኝነት የፈለገውን ሀብት ማግኘት ይችላል።"

# የሀብት ሳይንስ

## The Science of Getting Rich & The Science of Being Great




ዋላስ ዲ. ዋትልስ

ትርጉም፦ መለሰ እሸቱ

“ሀብታም የመሆን ሳይንስ አለ፤ እሱም እንደ አልጄብራ ወይም የሂሳብ አይነት ትክክለኛ ሳይንስ ነው። ማንኛውም ሰው ሳይንሱን ቢማር በእርግጠኝነት የፈለገውን ሀብት ማግኘት ይችላል፡፡”

# የሀብት ሳይንስ

## The Science of Getting Rich & The Science of Being Great




ዋላስ ዲ. ዋትልስ

ትርጉም፦ መለሰ እሸቱ

ⓜ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
© All Rights Reserved

የመጀመሪያ እትም ሰኔ 2013 ዓ.ም

**እነሆ ስጦታ፡-**

ለ ________________

ይህ **የሀብት ሳይንስ** የተሰኘው መጽሐፍ ሳይንሳዊውን የሀብት መንገድ እንዲያሳይህ/ሽ፤ እንዲሁም **የታላቅነት ሳይንስ** መጽሐፍ ደግሞ በሁሉ የተሟላ ታላቅነትን እንዲያጎናጽፍህ/ሽ በመመኘት ተበረከተ።

# ምስጋና

የሀብትና የመትረፍረፍን ጥበብ ለሰው ልጆች ላካፈለ ሁሉ ምስጋና ይሁን። ዋላስ ዋትልስ ደግሞ የተትረፈረፈ እና እየጨመረ የሚሄድን ሕይወት እንድንፈልግ ግልጽ በሆነ ቋንቋ ጥበብን ካካፈሉን ሰዎች ግንባር ቀደሙ ነውና መመስገን ይገባዋል። የምንፈልገውን ሁሉ እናገኝ ዘንድ ሕይወት እጅግ ባለጸጋና ለጋስ ነች። የተሟላና ደስተኛ ሕይወትን መፈለግ ደግሞ የሰው ልጅ ሊኖሩት ከሚችሉት ግቦች ሁሉ የተቀደሰው ነው። የዚህ መጽሐፍ አንባቢዎችም ሳይንሳዊውን የሀብት መንገድ ይዘውታልና መመስገን ይገባቸዋል።

ተርጓሚው

# ማውጫ

**እንደመንደርደሪያ**

ከምስጢሩ ጀርባ ያለው ምስጢር ........ 9

## መጽሐፍ አንድ

## የሀብት ሳይንስ

**መቅድም** ........ 12

**ምዕራፍ አንድ**

ሀብታም የመሆን መብት ........ 14

**ምዕራፍ ሁለት**

ሀብታም የመሆን ሳይንስ አለ! ........ 18

**ምዕራፍ ሶስት**

እድሎች ሁሉ በጥቂቶች እጅ ወድቀዋልን? ........ 23

**ምዕራፍ አራት**

ሀብታም በመሆን ሳይንስ ውስጥ የመጀመሪያው መርህ! ........ 28

**ምዕራፍ አምስት**

የሚጨምር ሕይወት ........ 35

**ምዕራፍ ስድስት**

ሀብት ወደ እናንተ የሚመጣበት መንገድ ........ 42

**ምዕራፍ ሰባት**

አመስጋኝነት ........ 48

**ምዕራፍ ስምንት**

በተወሰነ መንገድ ማሰብ ........ 52

**ምዕራፍ ዘጠኝ**

የፈቃድ አጠቃቀም ........ 57

**ምዕራፍ አስር**

ተጨማሪ የፈቃድ ኃይል ጥቅም ..................... 63

**ምዕራፍ አስራ አንድ**

በተወሰነ መንገድ መተግበር ..................... 70

**ምዕራፍ አስራ ሁለት**

ውጤታማ ተግባር ..................... 77

**ምዕራፍ አስራ ሶስት**

ወደ ትክክለኛው የስራ መስክ መግባት ..................... 83

**ምዕራፍ አስራ አራት**

እየጨመሩ የመሄድ ስሜት ..................... 88

**ምዕራፍ አስራ አምስት**

የእድገት ሰው ..................... 93

**ምዕራፍ አስራ ስድስት**

ጥቂት ማሳሰቢያዎች እና የመደምደሚያ እይታዎች ..................... 98

**ምዕራፍ አስራ ሰባት**

ሀብታም የመሆን ሳይንስ ማጠቃለያ ..................... 104

## መጽሐፍ ሁለት

## የታላቅነት ሳይንስ

**ምዕራፍ አንድ**

ማንኛውም ሰው ታላቅ ሊሆን ይችላል ..................... 108

**ምዕራፍ ሁለት**

የዘር ውርስ እና እድል ..................... 112

**ምዕራፍ ሶስት**

የኃይል ምንጭ ..................... 116

**ምዕራፍ አራት**

የእግዚአብሔር አእምሮ ..................... 119

**ምዕራፍ አምስት**

መዘጋጀት ....... 123

**ምዕራፍ ስድስት**

ማህበራዊ እይታ ....... 126

**ምዕራፍ ሰባት**

ግለሰባዊ እይታ ....... 131

**ምዕራፍ ስምንት**

መለየት ....... 134

**ምዕራፍ ዘጠኝ**

መለያ ማድረግ ....... 138

**ምዕራፍ አስር**

ምናብ መፍጠር ....... 142

**ምዕራፍ አስራ አንድ**

እውን ማድረግ ....... 145

**ምዕራፍ አስራሁለት**

ጥድፊያ እና ልማድ ....... 149

**ምዕራፍ አስራ ሶስት**

ሀሳብ ....... 153

**ምዕራፍ አስራ አራት**

ከቤት የሚጀምር ተግባር ....... 157

**ምዕራፍ አስራ አምስት**

የውጭ ተግባር ....... 161

**ምዕራፍ አስራስድስት**

ተጨማሪ ማብራሪያ ....... 166

**ምዕራፍ አስራ ሰባት**

ተጨማሪ ስለ ሀሳብ ....... 169

**ምዕራፍ አስራ ስምንት**

ታላቅነትን በተመለከተ የኢየሱስ ሀሳብ ..... 174

**ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ**

የዝግመተ ለውጥ ምልከታ ..... 178

**ምዕራፍ ሀያ**

እግዚአብሔርን ማገልገል ..... 181

**ምዕራፍ ሀያ አንድ**

የአእምሮ ልምምድ ..... 185

# እንደመንደርደሪያ
# ከምስጢሩ ጀርባ ያለው ምስጢር

ይህ የሀብት ሳይንስ በሚል ርእስ ተተርጉሞ የቀረበው መጽሐፍ የታዋቂው አሜሪካዊው ዋላስ ዋትልስ መጽሐፍት የሆኑት "ዘ ሳይንስ ኦፍ ጌቲንግ ሪች" እና "ዘ ሳይንስ ኦፍ ቢንግ ግሬት" በአንድ ላይ ሆነው የቀረቡበት ስራ ነው። መጽሐፍቶቹ ለርሆንዳ ባይረን፣ ለናፖሊዮን ሂል፣ ጆሴፍ መርፊ፣ ቦብ ፕሮክተር እና ለሌሎችም የፐርሰናል ዴቨሎፕመንት፣ ፋናንስ እና ስኬት መጽሐፍት ጸሐፊያን እንዲሁም በአለም ዙሪያ ለሚያካሂዷቸው የፐርሰናል ዴቨሎፕመንት ስልጠናዎች በእጅጉ መሰረት መሆን የቻሉ ናቸው።

እነዚህ የዋትልስ መጽሐፍት ከፍተኛ ሽያጭ ያስመዘገቡ ከመሆናቸውም በላይ እስካሁን ድረስ ከ80 በላይ በሆኑ የተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉመው ለገበያ ቀርበዋል። በተለይ "ዘ ሳይንስ ኦፍ ጌቲንግ ሪች" የተሰኘው መጽሐፍ ለተለያዩ ታዋቂ አለም አቀፍ የፐርሰናል፣ ፋይናንስ እና ስኬት አሰልጣኞች እንደ መሰረታዊ መመሪያ ከማገልገሉ ባሻገር ለበርካቶች የግል ሕይወት እና የቢዝነስ ስኬት አስተዋጽኦ ለማድረጉ በርካታ ምስክርነቶችን ማግኘት ችሏል።

THE SECRET በሚል ርእስ ፊልምና መጽሐፍ በማሳተም ዝናዋ የገነነው አውስትራሊያዊቷ ርሆንዳ ባይረን መጽሐፉ ለሕይወቷ መለወጥ እንዴት ምክንያት ሊሆን እንደቻለ እንዲህ በማለት በራሷ ቃላት ትገልጻለች፡-

*"ከሁለት አመታት በፊት በርካታ የሕይወት ተግዳሮቶች ገጥመውኝ ነበር። በቢዝነስ፣ በግንኙነት፣ በቤተሰብ ሕይወቴ ተግዳሮቶች ከበውኝ ባለበት ሰአት ከዚህ መጽሐፍ ጋር ተገናኘሁ። መጽሐፉን ካነበብኩባት*

ሌሊት ጀምሮ የድሮዋ እኔ አልነበርኩም፤ ሙሉ በሙሉ ተለውጬ ነበር። በሕይወቴ የሆነው ታላቅ ነገር እንዴት ሊሆን እንደቻለ መጽሐፉን ካነበባችሁት በኋላ ይገባችኋል።"

ታዋቂው የፐርሰናል ፋይናንስ እና ዴቨሎፕመንት አሰልጣኝና ደራሲ የሆነው ቦብ ፕሮክተርም በርሆንዳ ባይረን ሕይወት ውስጥ ለተከሰተው አስደናቂ ለውጥ ምክንያት የሆነውን የዋላስ ዋትልስ መጽሐፍ *ከምስጢሩ በስተጀርባ ያለ ምስጢር* ሲል ይገልጸዋል።

እነሆ ለናፖሊዮን ሂል፣ ጆሴፍ መርፊ፣ ቦብ ፕሮክተር እና ርሆንዳ ባይረን... እና ለሌሎችም የፐርሰናል ዴቨሎፕመንት አሰልጣኞችና ጸሐፊያን የጀርባ አጥንት የሆነውና THE SECRET (ምስጢሩ) ለተሰኘው መጽሐፍና ፊልም መፈጠር ምክንያት የሆነው ከምስጢሩ በስተጀርባ ያለው የሀብት ሳይንስ ምስጢር...

መልካም ንባብ

## መጽሐፍ አንድ

# የሀብት ሳይንስ

THE SCIENCE OF GETTING RICH

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ ተግባራዊ የሚያደረግ እንጂ ፍልስፍናዊ አይደለም፣ የተግባር መመሪያ እንጂ በጽንሰ ሀሳቦች ላይ የተመሰረተ ዝርዝር ጽሁፍ አይደለም። የተዘጋጀውም ከምንም ነገር በላይ ገንዘብ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶችና ወንዶች ነው- ከመፈላሰፋቸው በፊት ሀብታም ለመሆን ለሚፈልጉ። ይህ መጽሐፍ የሜታፊዚክስ ጥናት ውስጥ በጥልቀት ለመግባት መንገዱም፣ እድሉም ላልነበራቸው፣ ውጤትን ለሚፈልጉና ዝርዝር ጥናት ውስጥ ሳይገቡ ሳይንሳዊ የተግባር እርምጃ መደምደሚያዎችን ለመቀበል ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ነው።

አንባቢው በኤዲሰን ወይም በማርኮኒ የተገኙ የኤሌክትሪክ አሰራር ህጎችን እንደሚቀበለው ሁሉ፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተቀመጡትን መሰረታዊ መግለጫዎች በበጎ እምነት እንዲቀበል ይጠበቃል። የተሰጡትን መግለጫዎች በእምነት በመውሰድ እና ያለምንም ፍርሃት እና ማመንታት የተግባር እርምጃ በመውሰድ እውነትነታቸውን ማረጋገጥ ይቻላል። ይህንን የሚያደርግ እያንዳንዱ ወንድ ወይም ሴት በእርግጥ ሀብታም ይሆናል- በዚህ ውስጥ ያለው ሳይንስ ሊወድቅ የማይችል ትክክለኛ ሳይንስ ነው። ነገር ግን የፍልስፍና ንድፈ-ሀሳቦችን መመርመር ለሚፈልጉ እና ለእምነታቸው አመክንዮአዊ መሠረት እንዲኖራቸው ለማድረግ ለሚልጉ ግን የተወሰኑ ምንጮችን እጠቅሳለሁ።

አሀዳዊው የአጽናፈ ዓለም ጽንሰ-ሀሳብ አንዱ ሁሉም ነው፣ ሁሉም ደግሞ አንድ ነው ይላል። ይህ አንዱ ንጥረ-ነገር በቁስ አካላዊው ዓለም ውስጥ በብዙ ነገሮች መልክ ይገለጻል የሚለው ሀሳብ የሂንዱ መሰረት ያለው ነው። ይህም አስተሳሰብ በሂደት ወደ ምዕራቡ ዓለም መስፋፋት ከጀመረ ሁለት መቶ አመታት ይሆኑታል። ይህም ጽንሰ ሀሳብ የሁሉም የምስራቅ ፍልስፍናዎችና የዴስካርት፣ ስፒኖዛ፣ ሊብኔዝ፣ ሾፐንሀውር፣ ሄግልና ኤመርሰን ፍልስፍና መሰረት ነው። የዚህን መጽሐፍ የፍልስፍና

መሰረት ቆፍሮ ለማግኘት የሚፈልግ አንባቢ የሄግልና ኤመርሰን ስራዎችን እንዲያነብ ይመከራል፡፡

ይህንን መጽሐፍ ሳዘጋጅ ሁሉም ሰው በቀላሉ መገንዘብ እንዲችል ግልጽ እና ቀላል አቀራረብን ለመከተል የቻልኩትን ሁሉ አድርጌያለሁ፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ የተቀመጠው የድርጊት መርሃ ግብር ከፍልስፍና መደምደሚያዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በጥሩ ሁኔታ ተፈትኗል፡፡ በከፍተኛ ሁኔታ በተግባር ተፈትኖም ውጤትን አስገኝቷል፡፡ መደምደሚያዎቹ ላይ እንዴት መድረስ እንደተቻለ ማወቅ የምትፈልጉ ከሆነ ከላይ የጠቀስኳቸውን ምንጮች አንብቡ፡፡ የእነዚህን ሰዎች የፍልስፍና ፍሬ ለመሰብሰብ ከፈለጋችሁ ይህንን መጽሐፍ አንብቡና የሚሰጣችሁን መመሪያ በተግባር ላይ አውሉ፡፡

ደራሲው




# የሀብት ሳይንስ




“ጸሐፊው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉ እያንዳንዱ ምዕራፎች እንዴት የአእምሮ ገደቦችን ጥሰን በማለፍ የተሰወረውን ሀብት እንደምናገኝ (እንደምንሰብ) ያሳየናል።”

-ዩስኤ ቱደይ-

“የመጽሀፉን ገጾች እየገለጥኩ ሳነብ በከፍተኛ ጉጉት ነበር። የእንባ ዘለላዎቼ በመጽሐፉ ገጾች ላይ ይወርዱ እንደነበርም አስታውሳለሁ። የምስጢሩን ጨረፍታ እንድመለከት አድርጎኛል። በልቤ ውስጥ የሚቀጣጠል ነበልባል ይሰማኛል። ከዛን ቀን ጀምሮ የሆነውን ሁሉ ለዓለም ለማካካል ከፍተኛ ጉጉት አደረብኝ።”

-ርሆንዳ ባይረን-

የዘ ስክሬት መጽሀፍና ፊልም ደራሲ እና አዘጋጅ

“የሀብት ሳይንስ የተሰኘው ይህ የዋላስ ዋትልስ ስራ ለሮሀንዳ ባይረን ዘ ሴክሬት የተባለው መጽሐፍና ፊልም መነሻ መሆኑን ስንሰማ በጣም ተደንቀን ነበር። ርሆንዳ ባይረን ይህን መጽሐፍ ተአምራዊ በሚመስል መንገድ እንዴት ልታገኘው እንደቻለችና ሌሊቱን ሙሉ ከጥግ እስከጥግ እንዴት ስታነበው እንዳደረች ገልጻልናለች። ቢዘያች ሌሊት ለእኔና ለመጨረሻ ጊዜ ሕይወቷ ተቀየረ። ይህ የሀብት ሳይንስ መጽሐፍ በእኛም ሕይወት ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል።”

-ቦብ ፕሮክተር-

የላይፍ ሰክሰስ መስራች እና የፕርሰናል ዴቨሎፕመንት መጽሀፍት ደራሲ

ድህነትን ለማወደስ የተፈለገውን ያህል ቢባልም፣ እውነታው ግን አንድ ሰው ሀብታም ካልሆነ ወይንም በቂ ገንዘብ ከሌለው የተሟላ ወይም የተሳካ ሕይወት ሊኖር አይችልም።

ማንኛውም ሰው ሁለትና ሁለትን አባዝቶ አራትን አለማግኘት እንደማይችለው ሁሉ፣ ማንኛውም ሰው ለሀብት ሳይንሳዊ ህጎች እስከተገዛ ድረስ ሀብታም አለመሆን አይችልም!!

ዋላስ ዲ. ዋትልስ

BOOK LAND
0922740202
EIDO ADVERT

ዋጋ 180.00 ብር
ዋጋ አንድ መቶ ሰማኒያ ብር

ድራጋን ማተሚያ ቤት 0965677051